# ሰሞነኛ አጀንዳ

# በየት በኩል ተገናኙ?

አለባቸው ደሴ (ካዲስ አበባ መጋቢት 13 ቀን 2010)

ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነኝ ፃድቃን ገ/ትንሳይ (ሌተ/ጀነራል) እና አቶ ልደቱ አያሌው በአንድ ሳምንት ልዩነት በሪፖርተር ጋዜጣና በኤፍኤም ሬድዮ ጣቢያ ስለሰጡት በአገራችን የነፃ ኮሚሽን ይቋቋም አስተያየት/ምክር/አቋም ነው፡፡

በአንድ አገር ውስጥ የተለያዩ ይዘት ያላቸው ቀውሶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ቀውሶች፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ ወዘተ… ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የተለያየ ክብደትና መልክ ቢኖራቸውም ቀውሶች በአገሮች፣ በኩባንያዎች ወይም በፓርቲዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡

በዘርፉ ያሉ ምሁራን እንደዚህ ዓይነት ቀውስ በሚያጋጥሙበት ጊዜ ቀውሱን መፈታት የሚቻልበት አግባብ ብለው የሚያስቀምጡት ሃሳብ "የቀውስ አስተዳደር" "Crisis Management" ሊኖር ይገባል የሚል ነው፡፡ ይህም የተደራጀ የቀውስ አስተዳደር እቅድ በማስቀመጥ ቀውሱን ማስቀረት/ማስወገድ ወይም ከፍተኛ አደጋ እንዳይደርስ መከላከል የሚቻልበት ሁኔታ መፍጠር ይቻላል፣ ያስፈልጋልም ይላሉ፡፡

ስለሆነም ቀውሱን ለመቆጣጠር የቀውስ አስተዳደር እቅድ የሚያስፈልግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የእቅዱ ዝርዝር ግን እንደቀውሱ ደረጃ በይዘት፣ በጊዜ፣ በሚሳተፉት አካላት ደረጃ የሚወሰን ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ያጋጠመው የፖለቲካ ቀውስ በሌሎች አገሮች ካጋጠመው ቀውስ በመሰረቱ የተለየ አይደለም፡፡ ቀውሱ ለምንና እንዴት መጣ? በሚለው ዙርያ የተለያዩ ሃሳቦች ሊነሱ ይችላሉ፤ መነሳታቸውም አግባብነት አለው፡፡ ስለሆነም አሁን በአገራችን ያጋጠመውን ቀውስ ለመፍታት የቀውስ አስተዳደር ዝርዝር እቅድ ማዘጋጀትና ይህን የሚያስፈፅም አካል በአገር ደረጃ በማቋቋም ሊሰራ ይገባል፡፡

ለተፈጠረው ቀውስ መፍትሄ የሚሆን ሃሳብ ለማስቀመጥ የሚሞክር ግለሰብ ወይም ድርጅት መፍትሄ የሚለውን ሃሳብ ከማቅረቡ በፊት ግን የቀውሱን ሁኔታ በአግባቡ ማስቀመጥ (Define the Crises) ደረጃውን መለየት፣ አንድምታውን ማወቅ፣ የቀውሱን መንስኤዎችን በዝርዝር መለየት ይጠበቅበታል፡፡

ይህንን ማድረግ ቀውሱን ለመፍታት አንድ እርምጃ ወደፊት ያራምዳል ተብሎ የሚታመንበት ከመሆኑም ሌላ፣ ከአንድ ቀውስ ወደ ሌላ ቀውስ ላለመሸጋገር ማረጋገጫ ይሆናል ተብሎም ይታሰባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህን

ማድረግ ከጥላቻ፣ ከስሜታዊነት፣ ከአስፈፃሚነት (ተላላኪነት) ከአጭር ጊዜ እይታ በመራቅ ሚዛናዊና ሳይንሳዊ የሆነ የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥም ስለሚጠቅም ነው፡፡

አሁን በአገራችን ለተፈጠረው ቀውስ መፍትሄ ይሆናል ብለው የሚያስቡ ወገኖች ወይም ፓርቲዎች የተለያዩ ሃሳቦች እያቀረቡ ነው፡፡ ይህን ማድረጋቸውም አገራችን ወደ ከፋ ችግር እንዳትገባ ከማሰብ የመነጨ ቀና ሀሳብ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አንድ ቀውስ በተለይ ፖለቲካዊ ቀውስ ለመፍታት በምናስብበት ጊዜ አካሄዱ ከሁሉም በፊት ዴሞክራሲያዊና የሕግ የበላይነትን ባረጋገጠ መልኩ ቢከናወን ውጤቱም ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፡፡

ቀውሱ የሕግ የበላይነት ባረጋገጠ መልኩ መፈታት አለበት ሲባል በአገሪቱ ያለው ሕግና ስርዓት በጠበቀ መልኩ መሆን አለበት ማለታችን ነው፡፡ በአገሪቱ ያለው ሕግና ስርዓት እንዲሁም ይህን ለማስፈፀም በሕግ የተመሰረቱ ተቋማትን (Institutions) ወደ ጎን በመተው የሚደረግ የቀውስ አፈታት መንገድ ሌላ ቀውስ እንዲፈጠር ከማድረግ በቀር መጀመሪያ የተፈጠረውን ቀውስ አይፈታውም፡፡

ባለፈው ሳምንታት በወጣው የሪፖርተር እንግሊዝኛ ጋዜጣ ፃድቃን ገ/ትንሳይ (ሌተ/ጀነራል) እንዲህ ብለው ነበር፡፡

". . . Called for the establishment of independent commission to prepare a level political playing field for the upcoming election” . . . under the president.

ማለት የሚቀጥለውን ምርጫ ለማካሄድ እና የምርጫ ምሕዳሩን ለማመቻቸት በፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ስር ነፃ የሆነ ኮሚሽን ይቋቋም ይላል፡፡ ለዚህ ድምዳሜ አደረሰኝ የሚሉት መነሻ ምክንያት አሁን የተፈጠረው ቀውስ አገሪቱን እያስተዳደረ ካለው ፓርቲ (ኢህአዴግ) አቅም በላይ ሆኗል ከሚል የሚነሳ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ፃድቃን ገ/ትንሳይ (ሌተ/ጀነራል) ነፃ ኮሚሽን ይቋቋም የሚል የመፍትሄ ሃሳብ ካቀረቡ ከአንድ ሳምንት በኋላ ደግሞ አቶ ልደቱ አያሌው በሚዲያ “ነፃ ኮሚሽን በአዋጅ መቋቋም አለበት” ብለው ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

የእነዚህ ሁለት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ያገባናል፣ ባለቤት ነን፣ በዘርፉ እውቀት አለን ብለው የሚንደረደሩ ሰዎች ሃሳብ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የነፃ ኮሚሽን ይቋቋም አቋም በአጋጣሚ የመጣ ወይም የተነሳ ሃሳብ ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡ ከአንድ አቅጣጫ በአንድ ቡድን አማካይነት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጣልቃ በሚገባ ሃይል የተጠነሰሰ መልእክት እንደሆነ ለመገመት አያስቸግርም፡፡

ይህች አገር ላለፉት ከ20 በላይ ለሆኑ አመታት የምትተዳደርበት እና የምትመራበት ሕገ መንግስት አላት፡፡ ከደርግ ውድቀት በኋላ የምትገዛውም በዚህ ሕገ መንግስት ነው፡፡

አገሮች እየተበታተኑ ወደ እስር በርስ ውጊያ እየገቡ ያሉት ሕገ መንግስትና በህገ መንግስቱ መሰረት የቆሙ ተቋማት መስራት ተስኗቸው ሕግና ስርዓት በመጥፋቱ ምክንያት እንደሆነ እያየን ነው፡፡

አሁንም በኢትዮጵያችን ውስጥ ያጋጠመውን ቀውስ ሕገ መንግስቱና በሕገ መንግስቱ መሰረት የቆሙ ተቋማትን ህልውና በመጠበቅ ብቻ ሊፈታ እንደሚገባውና እንደሚችልም ከሁሉም በፊት ማመን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ውጪ የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ አገሪቱን ወዳልታሰበ የባሰ ቀውስ የሚያስገባት ከመሆኑ በቀር ቀውሱን የሚፈታ አይሆንም፡፡

ጎረቤታችን ደቡብ ሱዳን የተናጠችውና አሁንም በመናጥ ላይ ያለችው ሕግና ስርዓት ስላልተከበረ ነው፡፡ ተቋማት የሉም፣ ምርጫ የለም፣ ሕገ መንግስት የለም፣ የመከላከያ ሃይሉ ከነፃ አውጪ ሀይል ወደ ዘመናዊ ጦር ሰራዊትነት የተሸጋገረ እና በሕግ የሚገዛ አይደለም፡፡ የአገሪቱ ስልጣን በሙሉ በፕሬዝዳንቱ መዳፍ ስር የወደቀ ስለመሆኑ እኛ ጎረቤት ቀርቶ ድፍን አለም ያውቀዋል፡፡

ፃድቃን ገ/ትንሳይ (ሌተ/ጀነራል) ደቡብ ሱዳን ከሱዳን ነፃነትዋን ከተጎናፀፈች በኋላ የእርሰዎ ቡድንና ለቡድኑ የገንዘብ ድጋፍ ሲያደርጉ የነበሩ አገሮች ካደረጋችሁት ዓመታትን ከፈጀ ጥናትና ምርምር በኋላ ጥናታችሁ ደቡብ ሱዳንን በሁለት እግርዋ ለማቆም ፋይዳ ሳይኖረው ቀርቶ አገሪቱ ወደባሰ ቀውስ ገብታ መተራመስ ስትጀምር አገሩን ጥላችሁ እንደወጣችሁ እዚህ ላይ ማስታወሱ ተገቢ ይሆናል፡፡

አቶ ልደቱም የመሰረቱትና ለበርካታ አመታት የመሩት ፓርቲ ለሁለት ተከፍሎ በቀውስ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ እየታወቀ በፓርቲያችው ውስጥ የተፈጠረውን ይህን አነስተኛ ቀውስ እንኳን መፍታት ተስኗችሁ ይልቁንም ባካሄዱት የሬዲዮ ቃለ ምልልስ በፓርቲያቸው ውስጥ የተፈጠረውን ቀውስ አምኖ ከመቀበል ይልቅ ችግሩን ወደ ሌላ አካል ለማላከክ መሞከር ከትዝብት በቀር ፋይዳ ያስገኘልዎት አይመስለኝም፡፡

ሁለታችሁም አሁንም በሂደት ላይ ባሉና ገና መፍትሄ ባላገኙ ቀውሶች ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሚና ነበረችሁ፣ አሁንም አላችሁ፡፡ ሁለታችሁም እጃችሁን ያስገባችሁበት ቀውስ (የደቡብ ሱዳን የርስ በርስ ጦርነትና የኢዴፓ ፓርቲ ለሁለት መሰንጠቅ) ለመፍታት ምን አስተዋፅኦ አበረከታችሁ? ምን ውጤትስ መጣ? ተብላችሁ ብትጠየቁ አጥጋቢ መልስ መስጠት የምትችሉ አይደላችሁም፡፡ ታድያ በአሁኑ ወቅት በአገራችን የተፈጠረውን

ቀውስ ለመፍታት የሚያስችል ሃሳብ ለማቅረብ ምን ሞራል አላችሁ? እንዴትስ ነው በእናንተ በኩል የቀረበውን የመፍትሄ ሃሳብ ፍቱን መድሃኒት ነው ብለን መቀበል የምንችለው?

ሕገ መንግስቱን ወደ ጎን በማድረግ ሌላ የምርጫ አካሄድ ስርዓት እና ተቋም መፍጠር አገሪቱን ወደ ዳግም ቀውስ ከማስገባት በስተቀር የአገራችን የፖለቲካ ጉዳይ ያገባናል፣ ሃላፊነትም አለብን ከሚሉ ፓለቲከኞች የሚጠበቅ የመፍትሄ ሃሳብ አይደለም፡፡

ባለው ህገ መንግስታዊ ስርዓት ውስጥ ሆኖ የተደፈጠጠ ህግ፣ የተረገጠ መብትና ነፃ ያልሆነ ህብረተሰብ እና አመለካከት ካለ ግን ነፃ እንዲሆንና እንዲስተካከል በመንግስት ላይ ጫና በመፍጠር ማስተካከልና ሁሉንም ዜጋ በእኩልነት የሚሳተፍበት ነፃና በዜጎች ተቀባይነት ያለው ምርጫ እንዲሆን ጥረት ማደረግ ያባት ነው፡፡ ለነገሩ ተቀባይነት የሚለው አባባል እንደኛ በመሳሰሉ አገሮች በምንም መልኩ ምርጫ በነፃነትም ቢያካሄዱ “ዳኞቹ” ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ህዝቦች ሳይሆኑ ባዕዳን በመሆናቸው ይቀበሉታል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ እንደማይቀበሉት የታወቀ ነው፣ እንዲቀበሉትም አይጠበቅም፡፡ ለምን? ቢባል በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ የማይተካ ድርሻ አለኝ የሚለውና በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ፖሊሲ መሰረት የሚመራ መንግስታችን ከነሱ ፍላጎት ያፈነገጠ ነውና ምንም ቢደረግ ሊቀበሉት አይችሉም፡፡

ስለሆነም ፃድቃን ገ/ትንሳይ (ሌተ/ጀነራል) በየጊዜው የሚያቀረቡዋቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ይዘት ይህችን አገር ወደ ባሰ ቀውስ የሚያስገቡ በመሆናቸው፣ ከአንድ ጫፍ እየተለቀቁ ተባዝተው አቋም መስለው የሚዘረገፉ የተዛነፉ ሀሳቦች አገራችንን ወደከፋ ቀውስ የሚገፏት እንዳይሆን በጥንቃቄና በሀላፊነት መንፈስ ለመንቀሳቀስ ጥረት ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል፡፡

በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የመሰልዎትን አስተሳሰብ በማራመድዎ የሚጠይቅዎት ማንም የለም፡፡ መጠየቅም እንዳለሌብዎት ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ በየጊዜው በሚያራምዱት የተውገረገረ አቋም በታሪክ ተወቃሽና ተጠያቂ ላለመሆን ጥንቃቄ ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም "Democracy is about consensus and the rule of law” ብለው ለእርሶዎም ለእኔም እነዛ የምናውቃቸው "የዴሞክራሲ አባቶች” አስተምረውናልና፡፡